

# አጫጭር መረጃዎች፡- የ COVID-19 ክትባቶች እና እርግዝና

## ስለ COVID-19 ክትባቶች እና እርግዝና ብዙ የተሳሳቱ መረጃዎች አሉ። አንዳንድ የታወቁ እውነታዎችን እናንሳ!

### የ COVID-19 ክትባቶች ከእርግዝና በፊት፣ በእርግዝና ወቅት እና በኋላ ደህንነታቸው የተጠበቁ ናቸው።

ክትባቱ በእርግዝና ወቅት ከከባድ የ COVID-19 በሽታ ለመከላከል በ American College of Obstetricians and Gynecologists (ACOG፣ የአሜሪካ የፅንስ እና ማህፀን ስፔሻሊስቶች ኮሌጅ) እና Centers for Disease Control and Prevention (CDC፣ የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል) ይመከራል።

### ነፍሰ ጡር ሴቶች በ COVID-19 ከተያዙ ለከባድ የበሽታ ስጋት እና ለተጨማሪ በሽታዎች የተጋለጡ ናቸው።

በእርግዝና ወቅት ወይም ከእርግዝና በኋላ በ COVID-19 በሃይል መታመም መተንፈሻ የሚያስፈልገው ህክምና፣ በእርግዝና ወቅት የሚያጋጥሙ ተጨማሪ ውስብስብ በሽታዎች፣ ቀኑ ያልደረሰ ወሊድ ወይም ልጅን ሞቶ የመወለድ አደጋን በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል።

### የ COVID-19 ክትባቶች የወሊድ ችግሮች፣ የፅንስ መጨንገፎች፣ ቀኑ ያልደረሰ ወሊድ፣ ሞቶ የሚወለድ ልጅን ወይም ሌሎች ተጨማሪ በሽታዎችን እንደሚያስከትሉ የሚያመለክት ማስረጃ የለም።

ነገር ግን፣ የ COVID-19 ሕመም እነዚህን ተጨማሪ በሽታዎች እንደሚያስከትል ይታወቃል።

### ጡት እያጠቡ ከሆነ መከተብ አስተማማኝ ነው።

የጡት ወተት ከ COVID-19 ኢንፌክሽን ለመጠበቅ እንዲረዳቸው በ 6 ወራቸው ለክትባት ብቁ እስኪሆኑ ድረስ አንቲቦዲዎችን ወደ ልጅዎ ሊያስተላልፍ ይችላል።


**የመረጃ ምንጮች፡-**

በእርግዝና ወቅት ወይም ጡት በማጥባት ጊዜ የ COVID-19 ክትባቶች (cdc.gov) | https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/vaccines/recommendations/pregnancy.html (እንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ፣ ኮሪያኛ፣ ቬትናምኛ፣ እና ቻይንኛ ብቻ)

ነፍሰ ጡር እና በቅርብ ጊዜ ነፍሰ ጡር የነበሩ ሴቶች | CDC | https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/need-extra-precautions/pregnant-people.html (በእንግሊዘኛ ብቻ)

የ COVID-19 ክትባት እና እርግዝና፦ ማወቅ ያለብዎት ነገሮች | ጆንስ ሆፕኪንስ ሕክምና | https://www.hopkinsmedicine.org/health/conditions-and-diseases/coronavirus/the-covid19-vaccine-and-pregnancy-what-you-need-to-know (በእንግሊዘኛ ብቻ)



Washington State Department of HEALTH

DOH 825-049 August 2023 Amharic



ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ በ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም በ civil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።



Vaccinate WA

CovidVaccineWA.org